# እያለፈ ነው ዘመኔ

እያለፈ ነው ዘመኔ ትዕዛዙን ሳልፈፅም ወየው ለኔ
በጠራኝ ጊዜ ምን እላለሁ ና ብሎ ወደኔ (፪)
በወጣትነቴ ሳልሠራ እያየሁ አለፈኝ ብዙ አዝመራ
ከእንግዲህ በመሥራት ጌታ ሆይ ልኑር ካንተ ጋራ (፪)
የማስብበት በየዕለቱ ንፁህ ልብ ስጠኝ አቤቱ
ከትእዛዝህ ውጭ በመኖር እንዳልቀር በከንቱ (፪)
እንደየሥራው ለመስጠት በግርማ መንግስቱ ሲመጣ
ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፈተና የወጣ (፪)
እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ የተማራችሁ ከቃሉ
ይመጣሉና በርሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ (፪)
ትዕግስትን በመያዝ ሁላችሁ እስከመጨረሻው ጠንክሩ
ያን ጊዜ ይሆናል በርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ (፪)

www.HolyTrinityEOTCNY.org